ከአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# አለርት በዘጠና ዓመታት ጉዞው !!

**ዳንኤል ዘነበ**

የተመሰረተው እ. ኤ. አ በ1922 ነው። በአፍሪካ የመጀመሪያው የሥጋ ደዌ፣ የሳንባ ነቀርሳ እና ማገገሚያ ማሰልጠኛ ማዕከል እንደሆነ ይነገርለታል። ሆስፒታሉ ከቆዳ እና ስጋ ደዌ ሕመም ጋር ተያይዞ በሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት እውቅናን አትርፏል። ከሕክምናው በተጨማሪ በጤና ዘርፍ በሚሰራቸው ምርምሮች እና በሚሰጠው የስልጠና አገልግሎት ይታወቃል። ከማዕከልነት ወደ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት በመሸጋገር በአሁን ወቅት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለመሆን በቅቷል። አንጋፋው የመላው አፍሪካ የሥጋ ደዌ፣ የሳንባ ነቀርሳ እና ማገገሚያ ማሰልጠኛ ማዕከል (አለርት)።

በሀገራችን ቀደም ካሉ ጊዜያት ጀምሮ ከስጋ ደዌ ጋር ለተያያዙ የጤና ችግሮች መፍትሔ በመስጠት ይታወቃል። በአፍሪካ አህጉርም በጤናው ዘርፍ ስሙ የገነነ፤ በብዙ ኢትዮጵያውያን ልብና አዕምሮ ውስጥ ዘወትር የሚታወስ ተቋም ጭምር ነው። የአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ በሚመለከት የሆስፒታሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ዶ/ር ሽመልስ ገዛኸኝን አነጋግረናቸዋል። ዋና ስራ አስኪያጅ የሰጡንን ማብራሪያ እንደሚከተለው አዘጋጅተነዋል።

### የአለርት ጅማሮ

አለርትን የመሰረቱት ቀዳማዊ አፄ ኃዳማዊሥላሴ ናቸው። ሆስፒታሉ ከቆዳ እና ስጋ ደዌ ሕመም ጋር ተያይዞ ማከምያ፣ ማስተማርያና የማገገሚያ አገልግሎት ለመስጠት በሚል ተቋቋመ። በወቅቱ በሀገራችን የስጋ ደዌ በሽታ አሳሳቢ የነበረ በመሆኑ፤ አፄ ኃይለስላሴ የስጋደዌ ችግርን በዘላቂነት ለመከላከል፣ ሕሙማኑ የሕክምና እርዳታ የሚያገኙበትን መንገድ ለማምጣት ያስባሉ።

ንጉሱ አሁን ዘነበወርቅ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ለስጋደዌ ሕሙማን አገልግሎት የሚሰጥ የሕክምና ማዕከል መቋቋም እንዳለበት ይወስናሉ። ሀሳባቸውን ዶክተር ቶማስ ላምቤ ለሚባል ሚስዮናዊ ያጋሩታል፤ እሱም የንጉሱን ፍላጎት በመረዳት እንቅስቃሴ ይጀምራል። በ1924 ዓ.ም በዶክተሩ አስተባባሪነትና በኢትዮጵያ መንግስት ጥረት የስጋደዌ ሕክምና ማዕከሉ ግንባታ እውን ለመሆን በቃ። ከሁለት ዓመት በኋላም የስጋደዌ ሕክምና ማዕከል በንጉሱ ሴት ልጅ ስም ልዕልት ዘነበወርቅ መታሰቢያ ሆስፒታል ተብሎ አገልግሎት ጀመረ።

እ.ኤ.አ በ1965 ዓ.ም ሆስፒታሉ የስጋደዌ ሕክምና አገልግሎት መስጠቱን የሰሙ የአፍሪካ መሪዎች ለንጉሱ አንድ ሀሳብ ያቀርቡላቸዋል። ' የስጋደዌ ሕክምና ሆስፒታሉ የአፍሪካ ማሰልጠኛ ማዕከል እንዲሆን ' ሲሉ፤ አፄ ኃይለስላሴም በሀሳቡ ይስማማሉ። የዓለም አቀፉ የስጋደዌ ኮሚቴም ለዚህ ድጋፍ በመስጠቱ፣ የዘነበወርቅ ሆስፒታል የመላው አፍሪካ የስጋደዌ መከላከያና የስልጠና ማዕከል ሊሆን ችሏል። ዘነበወርቅ የነበረውን መጠሪያ ስሙን ወደ አለርት (የመላው አፍሪካ የስጋ ደዌ ሕክምና፣ የመልሶ ማቋቋምና ማሰልጠኛ ማዕከል) ሊቀይር ችሏል።

### ከማዕከል ወደ ኮንፕሬንሲቭ ሽግግር

በዚህ መልኩ ከሀገራዊ የስጋደዌ ማዕከልነት ወደ አህጉራዊ ተቋምነትም የተሸጋገረው አለርት፣ በስልጠና እና በምርምር ስራዎች በአፍሪካ እየተስፋፋ የመጣውን የስጋ-ደዌ የጤና ችግር ተፅዕኖን ለመቀነስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ተቋሙ ከስጋ-ደዌ ሕክምና አገልግሎት ጎንለጎን፣ በዚህ ዘርፍ የሚሰጠው የማስተማርና ስልጠና አገልግሎት ለሀገራችንና ለአፍሪካ ሀገራት በርካታ የጤና ባለሙያዎችን አፍርቷል። በስልጠና ፕሮግራሞቹ የቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ተማሪዎችን እየተቀበለ በብቃት ያሰለጥናል።

በሌላ በኩል ከቆዳ በሽታዎች ጋር በተያያዘ ማዕከሉ ትልቅ ልምድን ያካበተ ሲሆን፤ በዚህም ተቋሙ ከተለያዩ ሀገራት ማለትም ከአፍሪካ፣ አሺንያ እና ደቡብ ኤስያ የሚመጡ የሕክምና ባለሙዎች ስልጠና የሚያገኙበት እና ጥልቅ ጥናትና ምርምሮች የሚካሄድበት ተቋም ነው። የዓለም አቀፉ የጤና ድርጅት/World Health Organization/ አለርትን "የአፍሪካ ማሰልጠኛ ማዕከል" የሚል እውቅና ሰጥቶታል።



ዶ/ር ሽመልስ ገዛኸኝ የአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻሳይዝድ ሆስፒታል ዋና ስራ አስኪያጅ ፤

አለርት በሂደት የአገልግሎቱን አድማስ በማስፋት ከማዕከልነት ወደ ኮንፕሬሄንሲቭ ጀነራል ሆስፒታልነት ተሸጋግሯል። በአሁኑ ወቅትም ለሁሉም ዓይነት ታማሚዎች አጠቃላይ የሕክምና አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። አገልግሎቶቹም ፕላስቲክ እና ሪኮንስትራክቲቭ ቀዶ ጥገና ሕክምና፣ የአጥንት ቀዶ ጥገና ሕክምና፣ የቆዳና የአባላዘር ሕክምና፣ የድንገተኛ እና ፅኑ ሕሙማን ሕክምና፣ የእናቶችና የጨቅላ ሕጻናት ሕክምና፣ የጠቅላላ ቀዶ ጥገና ሕክምና፣ የሕፃናት ሕክምና፣ የውስጥ ደዌ ሕክምና የጥርስ ሕክምና፣ የአይን ሕክምና፣ የስነ - አዕምሮ ሕክምና ናቸው።

### አለርትና ዐቢይ ስኬቶቹ

ከሀገራዊ የስጋደዌ ማዕከልነት ወደ አህጉራዊ ተቋምነትም የተሸጋገረው የአለርት አጠቃላይ ሆስፒታል፣ በስልጠና እና በምርምር ስራዎች በአፍሪካ እየተስፋፋ የመጣውን የስጋ-ደዌ የጤና ችግር ተፅዕኖን ለመቀነስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። አለርት ከስጋ-ደዌ ሕክምና አገልግሎት ጎንለጎን፣ በዚሁ ዘርፍ የሚሰጠው የማስተማርና ስልጠና አገልግሎት ለሀገራችንና ለአፍሪካ ሀገራት በርካታ የጤና ባለሙያዎችን አፍርቷል።

በስልጠና ፕሮግራሞቹ የቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ተማሪዎችን እየተቀበለ በብቃት ያሰለጥናል። በጤናው ዘርፍ ለሚገኙ ኃላፊዎች፣ መካከለኛ ባለሙያዎችና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችም እንዲሁም ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የተግባር ስልጠናዎችን በመስጠት የላቀ ድርሻ አበርክቷል። በዚህም በተለያዩ የጤና ዘርፎች ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በታማኝነት የሚያገለግሉ ብቁ ባለሞያዎችን በማሰልጠን ጉልህ ድርሻ አበርክቷል።

የአለርት ማዕከል ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያደርገው ድጋፍ ተማሪዎቻቸውን በተግባር በማሰልጠን የተገደበ አይደለም። ተቋማቱ በስጋደዌ ምርምር ላይ የሚያተኩሩ ፕሮግራሞችን እንዲያስጀምሩም ድጋፎችን ሲሰጥ ኖሯል። እንደ ምሳሌም፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቆዳ ሕክምና የድህረምረቃ ፕሮግራም እንዲጀምር ማዕከሉ ድጋፍ ሰጥቷል። ከዚህ አኳያ አለርት በጤናው ዘርፍ የማይደበዝዝ አሻራ አኑሯል። የአለርት ማዕከል በሕክምና እና ስልጠና ዘርፎች ከሚሰጠው ውጤታማ አገልግሎት በተጨማሪ በምርምር መስኩም ከኢትዮጵያ አልፎ ለአህጉሪቱ የተረፉ ስራዎችን አከናውኗል።

በምርምር ስራው በስጋደዌ፣ በቲቢና በሌሎችም በሽታዎች መንስኤና መፍትሔ ዙርያ የሚያጠነጥኑ ሳይንሳዊ ፅሁፎችን በየጊዜው እያሳተመ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል። በማዕከሉ ከተዘጋጁት የምርምር ፅሑፎች መካከል፣ 12 ዓመታትን ፈጅቶ በሊፕረሲ ሪቪው ጆርናል ላይ የወጣው ፅሑፍን ጨምሮ በየጊዜው የሚወጡ ጥናቶች ይጠቀሳሉ።

### የስኬት መዳረሻ አመላካች ጅማሮዎች

አለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በዘጠና ዓመት ጉዞው ያካበተውን ልምድ፣ ያዳበረውን አቅምና የፈጠረውን በጎ ተፅዕኖ በመጠቀም፣ ራሱን ወደ አዲስ የዕድገት ምዕራፍ የሚያሸጋግርበት ሂደት ውስጥ ገብቷል። በጤናው ዘርፍ እጅግ ዘመናዊ የልህቀት ማዕከል ለመሆን የሚያስችሉትን ስራዎች በስፋት እያከናወነ ይገኛል። በአለርት ሰፊ፣ ውብና ማራኪ ግቢ ውስጥ የተገነቡት ዘመናዊ ሕንፃዎች እንደየ ዓላማቸው በአግባቡ የተዘጋጁ፣ የተደራጁና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት በሚያስችሉ ዘመናዊ መሳሪያዎች የተሟሉ ናቸው። ሆስፒታሉ ስራዎቹን የሚያቀላጥፍባቸው የተለያዩ በኮምፒዩተር የተደገፉ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ባፈራቸው ቁሳቁሶች የተደራጁ ቤተሙከራዎች አሉት።

የሕክምና ባለሙያዎች፣ ሰልጣኞችና ሰራተኞች የሕክምና፣ የስልጠናና የምርምር ስራዎቻቸውን በመረጃ የሚያስደግፉባቸው ደረጃቸውን የጠበቁ አብያተ መጽሐፍት የማዕከሉ አቅም ማሳያዎች ናቸው። ሁሉም በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተደገፉ መሆናቸው ለአጠቃቀም ምቹ ያደርጋቸዋል።

በሌላ በኩል ተቋሙ ለማሳካት ያስቀመጠውን ራዕይና የቀየሰውን ግብ የሚያሳኩ ትላልቅ የመሰረተልማት ግንባታዎችና ማስፋፊያ በስፋት በመተግበር ላይ ናቸው። ከእነዚህ ስራዎች መካከልም፣ በሁሉም መልኩ የተሟላ፣ የዘመናዊ ሕክምና ተቋም ተምሳሌት የሆነ፣ ዘርፈ-ብዙ አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ በጥበብ ዲዛይን የተደረገ፣ የባለ 500 አልጋ ሆስፒታል ይገኙባቸዋል። አሁን ግንባታው በመገባደድ ላይ ሲሆን፤ ይህ ግዙፍ የሆስፒታል መሰረተልማት፣ ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉት ዘመኑ ባፈራቸው የሕክምና መሳሪያዎች የተሟላ፣ ሁሉንም ዓይነት የሕክምና መገልገያዎችን ያሟላ፣ በዘመናዊና ትላልቅ ላቦራቶሪዎች የታጠቀ ይሆናል።

የአዳዲስ ሕንፃዎች ግንባታና የመሰረተልማት ማስፋፋት ስራው፣ ሆስፒታሉ ከዚህ ቀደም ሲሰጥ የነበረውን የጥናትና ምርምር ተግባሩንም በበለጠ በጥራትና በብዛት ለማከናወን ያስችለዋል። በዕድሜው ያፈራውን እሴት በመጠቀም፣ በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ እውቀት፣ ክህሎትና ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎችን ማፍራትና በበሽታዎች ላይ መፍትሔ-ተኮር ምርምሮችን ማካሔድ አሁንም የአለርት ማዕከል ግንባር ቀደም ኃላፊነት ሆኖ ይቀጥላል።

ግንባታውና የማስፋፊያ ስራውም ይህን ታሳቢ ያደረገ ነው። የሕክምና አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋማት የሚጠበቀው፣ ሁለንተናዊ የግቢና የስራ አካባቢ ፅዳትና ውበት በአለርት ማዕከል ላቅ ባለ ደረጃ እየተሰራ ይገኛል። የስራ አካባቢው ለሌሎችም አርአያ በሚሆን መልኩ፣ በግቢም ይሁን በመገልገያ ክፍሎች፣ ለአይን በሚማርክ፣ ምቾትን በሚሰጥ መልኩ እየተከናወነ ነው። ይህ እንቅስቃሴ ለማዕከሉ ማሕበረሰብ፣ ለታካሚውና ለሰልጣኙ ሁሉ አካላዊ ምቾትን ከመለገስ፣ መንፈሳዊ እርካታን ከማጎናፀፍና አዝናኝ ድባብን ከመፍጠር አኳያ ፋይዳው ትልቅ ነው ።

### ተቋማዊ ሳንካዎች

የአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የአገልግሎት አድማሱን እንዲያሰፋ፣ የተገልጋዮችን ብዛት ለመጨመር፣ የአገልግሎት ጥራቱን ለማሻሻል፣ ተቋማዊ ብቃቱን ለማሳደግና አሰራሩን ለማዘመን የተለያዩ ጥረቶችን አድርጓል። ከእነዚህ መካከል በኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ማሻሻያ ፕሮግራም መሰረት የአለርት ሆስፒታልን አሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ለማሳደግ የተደረገው እመርታዊ አካሔድ ተጠቃሽ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ በርካታ ችግሮች አጋጥመውታል። እያጋጠሙትም ይገኛል።

በዋናነት በሆስፒታል ደረጃ በርካታ ታካሚዎችን ይዞ አገልግሎት በመስጠት በኩል በሀገሪቱ አንደኛ መሆኑ ይታወቃል። በተቋሙ የተገልጋይ ቁጥር ከመጨመር ጋር ተያይዞ የሚያጋጥሙ ችግሮች አሉ። እንዲሁም የመሰረተ ልማት በበቂ ሁኔታ ጋር አለመሟላት፣ የበጀት ችግር ተጠቃሽ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የማስፋፊያ ስራዎች በሚሰሩበት ወቅት ከመሬት ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ ችግሮች አሉ። በተቋሙ የመሬት ይዞታ በሆነ ቦታ ላይ በሕገወጥ መንገድ የተገነቡ ከ100 በላይ ቤቶች አሉ። ይህን ችግር ለመፍታት ከክፍለከተማው ጋር እየተነጋገርን ሲሆን፤ በቅርቡ መፍትሄ ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

### እንደ መውጫ

የመላው አፍሪካ የሥጋ ደዌ፣ የሳንባ ነቀርሳ እና ማገገሚያ ማሰልጠኛ ማዕከል (አለርት) አፍሪካን ያማከለ ግዙፍ ራእይ ይዞ የተነሳው ማዕከሉ የአህጉሪቱ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ሆኖ ለረዥም ጊዜ ዘልቋል። አለርት በተለይም በቆዳ ሕክምና ካለው ልምድ አንጻር "ሌላ ቦታ ያሉ ሀኪሞች ምስል አንስተው በሚያጋሩት ምስሎች ተንተርሶ በቴሌ-ኮንፈረንስ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። በዚህም ተቋሙ ከተለያዩ ሀገራት ማለትም ከአፍሪካ፣ አሺንያ እና ደቡብ ኤስያ የሚመጡ የሕክምና ባለሙዎች ስልጠና የሚያገኙበት እና ጥልቅ ጥናትና ምርምሮች የሚካሄድበት ተቋም ለመሆን በቅቷል።

በቀጣይ አለርት ከቆዳና ተያያዥ ሕመሞች ጋር በተያያዘ በአፍሪካ ደረጃ የልህቀት ማዕከል ሆኖ ለመውጣትና ያለውን ስም ለማስቀጠል እየሰራ ነው። ከጉዳት ጋር በተያያዙ ሕክምናዎች እንዲሁም በአካባቢያዊ በሽታዎች (Tropical diseases) ላይ ማዕከሉን የልህቀት ማዕከል ለማድረግ እንዲሁም የሜዲካል ቱሪዝም ስራዎችን ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል። በተጨማሪም አለርት ሰፊው ማህበረሰብ ተጠቃሚ የማድረግ ራእዩ እውን ኢንዲሆን ብቁ የሰው ኃይል ከማፍራት፣ የጥናትና ምርምሮች ጥራትና ብዛት ከፍ ከማድረግ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ግንኙነት ከማደስ አንጻር የሚሰራ ይሆናል።